# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፦** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

***ታህሣሥ 9 ቀን 2003 ዓ.ም.***

**በወያኔ ቡድን ውስጥ ትርምስ ተፈጠረ፤**

***ወያኔ ከባድ የጦር መሳሪያውን እና ጦሩን ወደ ሰሜንና ምስራቅ እያጉዋጉዋዘ መሆኑ ተጋለጠ፤***

**ለብሔር ቤሔረሰቦች በዓል በሚል በመቶ ሚሊዮን ብር ወጪ ተደረገ፤**

***ከተጋበዙት 30 መሪዎች ሁለት ብቻ ተገኙ፤***

ወያኔ ከተቃዋሚ ኃይሎች ሲጠብቀው የነበረው ተቃውሞ እና ንትርክ ሲረግብለት በውስጥ ድንገት ፈንድቶ ሲያመሰው እንደሰነበተ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ አጋለጠ። ሰሞኑን ለነባር እና ለአዳዲስ ከፍተኛ ካድሬዎቹ ስልጠና ሲሰጥ ያለመግባባት ተከስቶ በንትርክ፤ በጭቅጭቅ አልፎ ተርፎ በዛቻ መጠናቀቁን የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ እሁድ ታህሳስ 4 ቀን 2003 ዓ.ም በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ተገኝተው በፕላዝማ በመልካም አስተዳደር ፤የኪራይ ሰብሳቢነት መንገስ ፤የተደረገው መተካካት ትክክለኛነት እና በሌሎችም ጉዳዮች ዙሪያ በተሰጣቸው የአንድ ቀን ኮርስ ላይ በተነሳ ጥያቄ እርስ በርስ መግባባት ጠፍቶ ከድሬዎቹ ሲሰዳደቡና ሲዘላለፉ እንደዋሉ ታውቆዋል።

በየትምህርት ቤቶች መማሪያ ክፍሎች ውስጥ ተደረገ በተባለ የፕላዝማ ውይይት ከፍተኛ አመራር የተባሉት በሙሉ የችሎታ ማነስና በመልካም አስተዳደር ችግር የተዘፈቁ በመሆናቸው ሊነሱና በምትካቸው አዳዲስ እና ችሎታ ያላቸው ሊሾሙ ይገባል ያሉት ተሰብሳቢዎቹ መተካካት ተብሎ በቅርቡ የተሾሙትም ቢሆን ቀልድ እና ፌዝ እንጂ በትክክል አልተደረገም ሲሉ ቅሬታና ተቃውሞ ማቅረባቸው ታውቆዋል::

ያለ ችሎታቸው ከክልል ተነስተው በአንድ ግዜ ሚኒስትርነት ሲሰጣቸው መመዘኛው ምን እንደሆነ ለእኛ ለካድሬዎቹ ሳይነገርና ሳይገለፅልን የተፈፀመ ከመሆኑም ባሻገር ተሾሙ የተባሉትን ጀርባ ስንመለከት ዕውቀት እና ችሎታ የሌላቸው የብሔር ማሙያ ብቻ መሆኑን የተረዳን ስለሆነ በአስቸኳዋይ ማስተካከያ ይደረግበት ሲሉም የፀና አቋዋም መያዛቸው ታውቆዋል::

በአሁኑ ሰዓት ህዝብ ከመቼውም ግዜ በላይ በአመራሩ እየተበደለ እሮሮ እያሰማ ባለበት ሰዓት ጥሩ ስራ ተሰርቶዋል ተብሎ በየመገናኛ ብዙሀን መገለፁ የሚያሳዝን እና የሚያሳፍር ከመሆኑም በላይ ተማርን የተባልነው አዳዲስ አመራሮች የተሻለ ነገር እንድንሰራ መጣን እንጂ እንዲህ ያለ ተልካሻ እና የተዝረከረከ ስራ ለማየት እና ለማድመቅ አልመጣንም ሲሉ መረር እና ከረር ያለ አስታያየት መስጠታቸውም ተጠቁሞዋል::

በፕላዝማ ትምህርቱን ሲሰጥ የነበረው የአዲስ አበባ የወያኔ ከፍተኛ አመራር የሆነው ልዑልሰገድ የተባለው ከበረሀ የመጣው ካድሬ ሲሆን የአዳዲስ ካድሬዎቹን ጥያቄ መመለስ ተስኖት ግርድፍ ስድብ ከመሳደቡም በተጨማሪ የቁዋመጣችሁለትን ስልጣን አታገኙም ሲል የገዛ ካድሬዎቹን እንዳስፈራራቸው ታውቆዋል::

መንግስት እና ፓርቲ አምኖበት ስልጣን የሰጣቸውን ሚኒስትሮች እናንተ የማንኩዋሰስም ሆነ የማዋረድ መብት የላችሁም ያለው ይኼው ግለሰብ እናንተ በአቋዋራጭ ስልጣን ለመያዝ አቅዳችሁ የመጣችሁ እንጂ ለፓርቲው ስራ ስትሉ የመጣችሁ አይደላችሁም ሲልም ዛቻ ጭምር መሰንዘሩን የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

የውይይቱ ተሳታፊ ወጣት የወያኔ ካድሬዎች በቅርቡ ሚኒስትሮች ብቻ ሳይሆኑ አምባሳደር ሆነው የተሾሙትም ቢሆኑ በእድሜ ብዛት ስራ ከሚሰሩበት የማይሰሩበት ግዜ የሚበልጥ ከመሆኑም በላይ ሀገራዊ አጀንዳ ለማስፈጸም አቅም የሌላቸው ሆነው ሳለ አምባሳደር ተብለው መሾማቸው በሀገር እና በህዝብ መቀለድ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ሲሉም ጠንካራ አቋዋም ይዘው ሲከራከሩ እንደነበር ለማወቅ ተችሎዋል::

በመጨረሻም በፓርቲው ውስጥ የአመራር መተካካት ተብሎ እስከ አሁን የተደረጉት ሹም ሽረቶች የማስመሰል ስለሆነ እንደ አዲስ በእውቀት እና በችሎታ ብቻ እንጂ ለብሔር ተዋፅኦና ለኮታ ማሙያ መሆን የለበትም ሲሉም አፍለኛ የወያኔ ካድሬዎቹ ለከፍተኛ አመራሮቹ ማስጠንቀቂያ ጭምር የሰጡ ሲሆን ይህን ሁኔታ ተግባራዊ ካላደረጉ በአጭር ቀን መልቀቂያ እንደሚያስገቡና ለህዝብ ጉዳዩን እንደሚገልፁ ማስታወቃቸውን ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል::

በሁለቱ የወያኔ ቡድኖች መሀከል የተከሰተው ጭቅጭቅ እና ንትርክ መቋዋጫ ሳይበጅለት የተበተነ ቢሆንም ጉዳዩ አሳሳቢና አንገብጋቢ በመሆኑ ለመለስ ዜናዊ ቀርቦ በቅርቡ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል ተብሎ እየተጠበቀ ሲሆን ወጣት ካድሬዎቹ በበኩላቸው ዝም ብለው ለ20 ዓመታት በስልጣን ላይ ተቀምጠው እየተነዱ የመጡት የበረሀ አመጣሽም ሆነ ከተማ ሰርጎ ገብ ባለስልጣናት እውቀት እና ችሎታ የሌላቸው በመሆናቸው እስካልተስተካከለ ድረስ ስራ እንደማይሰሩ ጽኑ አቋዋም መያዛቸውን የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

በተያያዘ ዜና ግራ የተጋባው የወያኔ ቡድን ሰሞኑንም ጦሩን ከቦታ ወደ ቦታ እያጉዋጉዋዘ ከመሆኑም በተጨማሪ አዳዲስ ከባድ የጦር መሳሪያ ከውጭ በኮንቲነር እያሸገ ማስገባቱ ተጋለጠ::

ባለፈው ሳምንት ውስጥ በጅቡቲ ወደብ በኩል ምንነቱ ያልታወቀ የጦር መሳሪያ ተጭኖ በኮንቲነር ታሽጎ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ሲሆን ሀገር ውስጥ ደግሞ በሁለት አቅጣጫ ከባድ የጦር መሳሪያዎች እየተመሙ መሆኑን ከአይን እማኞች ለማረጋገጥ ተችሎዋል::

ይሄው ግዙፍ ከባድ የጦር መሳሪያ ከአዲስ አበባ ወደ ሰሜን የሀገሪቱ ክፍሎች በጎጃም እና በጎንደር በኩል ሰንጥቆ እያለፈ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በአዋሽ አድርጎ ወደ ምስራቅ ኢትዮጵያ እየተመመ መሆኑን ከዓይን እማኞች የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

በተለይ ከዓርብ ታህሳስ 1 ቀን እስከ ዕሁድ ታህሳስ 3 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ለሶስት ተከታታይ ቀናት ከባድ የጦር መሳሪያ በአየር መቃወሚያ ታጅቦ ከመሀል ሀገር ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ እየተመመ መሆኑን የአይን እማኞች አጋልጠው በወቅቱ ሲጉዋጉዋዙ የታዩት ታንክ፤ አየር መቃወሚያ ፤መድፍ እና አጫጭር ሮኬቶች ጭምር እንደነበረም የአይን እማኞቹ አልሸሸጉም::

ከህዝብ እይታ ውጭ በሆነበት ውድቅት ሌሊት እየተጉዋጉዋዘ የሚሄደው ይሄው የጦር መሳሪያ እጅግ በጣም ብዙ ከመሆኑም በላይ ከፊት እና ከመሀል እንዲሁም ከሁዋላ በወታደሮች እና መትረየስ በተጠመዱ መኪኖች እየተጠበቁ እንደሚሄዱ የታወቀ ሲሆን ቀን ቀን ሰው በማይታይበት ጫካ ውስጥ አስገብተው እንደሚያውሉዋቸውም ከአይን እማኞቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል::

በሁለቱ ሱዳኖች መሀከል ግጭት ሊቀሰቀስ ይችላል በሚል ሰበብ ወያኔ ከባድ የጦር መሳሪያዎቹን ወደ ድንበር ከማስጠጋቱም በተጨማሪ ሁለት እግረኛ ብርጌድ ውስጥ ውስጡን እንዳስጠጋና ሙሉ ለሙሉ የጎንደርን በረሀዎች ለመቆጣጠር እየተንቀሳቀሰ መሆኑን የመከላከያ ምንጮች አጋልጠዋል::

በምስራቅ ኢትዮጵያ በኩልም ያሉት ታጣቂ ሃይሎች ድንገተኛ ጥቃት እየሰነዘሩ በወያኔ ጦር ላይ ጉዳት እያደረሱ መሆኑን የጠቆሙት የመከላከያ ምንጮች እነዚህን ታጣቂ ኃይሎች በዘመቻ

ለመደምሰስ እና ሱማሊያንም በቅርብ ርቀት በከባድ መሳሪያ ለመቆጣጠር ሲባል ግዙፍ የጦር ኃይል አስቀድሞ የገባ ሲሆን ሰሞኑንም ከባድ የጦር መሳሪያ እየተጉዋጉዋዘ መሆኑን አጋልጠዋል::

በምስራቅ እና በሰሜን ያለው ውጥረት ከግዜ ወደ ግዜ እያየለ ባለበት በአሁኑ ሰዓት በመሀል ሀገር ውስጥም ህዝቡን በደህንነት መከታተል እና ማስጨነቁ እየተባባሰ የመጣ መሆኑ ታውቆዋል::

ሰሞኑን በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች ውስጥ ሰርገው የገቡ የታጣቂ ቢድኖች አሉ በሚል ደህንነቶችን ወደ ህዝቡ ውስጥ አሰማርተው ያሉ ከመሆኑም በተጨማሪ የፎረም አባሎቻቸውን ወደ የሰፈሩ ውስጥ እያስገቡ ህዝቡን እያመሱት መሆኑም ታውቆዋል::

በፓርኪንግ ስራ ላይ ያሰማሩዋቸው የፎረም አባሎችም የስለላ ስራ እንዲሰሩና ለየት ያለ ሰው ሲመለከቱ ሪፖርት እንዲያደርጉና ጥቆማ እንዲያቀርቡ ከየክፍለ ከተማው የደህንነት ኃላፊዎች ትዕዛዝ ተሰጥቶዋቸው እየሰሩ ሲሆን በቅርብ ርቀትም የሚቆጣጠሩዋቸው ደህንነት ሰራተኞች እንዳሉም አንዳንድ የፓርኪንግ ሰራተኛ ወጣቶች ለደንበኞቻቸው ሲነግሩ ተደምጦዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ወያኔ በህዝብ እና በሀገር ሀብት ላይ እየተጫወተ ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም አሁን ደግሞ በተለያዩ ሁኔታዎች መልኩንና ይዘቱን በመቀያየር እጅግ በሰፋና በከፋ ሁኔታ የሀገሪቱ ህዝቦች የእለት ጉርስ አጥተው እና የኑሮ ውድነት እግር ከወርች አስሮ እያንጋላታቸው ባለበት በአሁኑ ሰዓት በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ በማድረግ ካድሬዎቹን እና ባዕዳንን እያዝናና መሆኑን የተመለከቱ ህዝቦች እየተበሳጩ መሆኑ ታውቆዋል::

የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በሚል ለ15 ቀን በጮማና በውስኪ በየክልሎቹ ሲያንበሸብሻቸው ከርሞ ሰሞኑን ደግሞ መልሶ አዲስ አበባ ድረስ አስመጥቶ እንደገና ፌዴራሊዝም በዓል በሚል ድል ያለ ድግስ ደግሶ እየጋበዛቸው ከመሆኑም በተጨማሪ የውሎ አበል እየተሰጣቸው መሆኑን ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል::

ለ15 ቀናት በየክልል ከተሞች የራሱን ካድሬዎች እና ደጋፊዎች በጮማና ውስኪ ከማንበሻበሹም በተጨማሪ ጠቀም ያለ የኪስ ገንዘብ እየሰጣቸው ሲዝናኑ የሰነበቱ ሲሆን በአንጻሩ ህዝቡ የሚቀምሰው አጥቶ ለከፍተኛ ችግር ተዳርጎ ይገኛል::

የክልሉን ድግስ ጠግበው ካለፈው ሳምንት ሰኞ ዕለት ጀምሮ ደግሞ ከሁሉም ክልሎች ተውጣጥተው የመጡ ናቸው የተባሉ ቁጥራቸው በሺህዎች የሚቆጠሩትን ካድሬዎች እና አጨብጫቢዎች አዲስ አበባ ትላልቅ ሆቴል ተይዞላቸው እጅግ ውድ በሆኑ ሆቴሎች እየተዝናኑ ከመሆኑም ባሻገር ውሎ አበል፣ መኝታ፣ ምግብ እያለ በቀን ለአንድ ሰው ከ500 ብር በላይ ወጪ መመደቡን ለማወቅ ተችሎዋል::

የሀገሪቱ ህዝቦች በየቀኑ በሚንረው ኑሮ ውድነት ግራ ተጋብተው እያሉ ወያኔ ለፖለቲካው መጠቀሚያ ሲል ብቻ በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ አድርጎ እዚህ ግቡ የማይባሉትን እንቶ ፈንቶዎችን እያዝናና መሆኑን የተረዱት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በወያኔ ተግባር እጅግ ከማዘናቸውም በላይ እየተበሳጩ ነው::

አንዱ በዓል ሲያልቅ ሌላ በዓል እየፈጠሩ የሚዝናኑት የወያኔ ሹምንቶች የብሔር ብሔረሰቦች በዓል በሚል ከ20 ቀናት በላይ ሲጨፍሩና ሲያውደለድሉ ከርመው እንደገና ደግሞ ሰሞኑን የፌዴራሊዝም ስርዓት በሚል በተዘጋጀ ጉባዔ ላይ በሚሊኒየም አዳራሽ ድል ያለ ድግስ ተደግሶ በህዝብ ገንዘብ እና በሀገር ሀብት ሲጫወቱበት ከርመዋል።

ከክልል መስተዳድር እስከ ወረዳ አስተዳዳሪ...... ከደህንነት ሹማምንት እስከ ጆሮ ጠቢ..... ከደጋፊ ባለሀብት እስከ ልማታዊ ጋዜጠኛ ድረስ የወያኔን ፖለቲካ የሚያስተጋቡ ከ20 ሺህ በላይ ካድሬዎች ተሰብስበው ሰኞ ዕለት ታህሳስ 4 ቀን 2003 ዓ.ም ከቀኑ 10 ሰዓት እስከ ውድቅት ሌሊት ድረስ በሚሊኒየም አዳራሽ በተደረገላቸው ግብዣ በጮማና በብላክ ሌብል ውስኪ ሲንበዛበዙ ነበር ያመሹት።

የፌዴራሊዝም ስርዓት የሚያራምዱ ሀገራት ጉባዔ ለማዘጋጀት ደጅ ጠንቶ የተሰጠው ወያኔ ዝግጅቱን በህዝብ ሀብት እና ገንዘብ ቢያደምቅም ከአፍሪካም ሆነ ከሌሎች ክፍለ ዓለማት መሪዎች ሳይገኝ ፦ በመቅረታቸው ቡድኑ ያሰበው ሳይሳካ መቅረቱ ታውቆዋል።

በጉባዔው ላይ ከ30 በላይ የሀገር መሪዎች ይገኛሉ ተብሎ በነመለስ ዜናዊ ሽብ ረብ ተብሎ ዝግጅት ቢደረግም ከቁብ ያልቆጠሩት የአፍሪካም ሆነ የሌሎች ክፍለ ዓለማት ሀገር መሪዎች ሳይገኙ ከመቅረታቸውም በተጨማሪ ተቀማጭነታቸው እዚሁ አዲስ አበባ የሆኑትን ዲፕሎማቶቻቸውን ብቻ እንዲወከሉ በማድረጋቸው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ መበሳጨቱ ታውቆዋል።

ከአፍሪካ በዘር ማጥፋት ወንጀል በዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት የሚፈለገው የሱዳኑ ፕሬዝዳንት አልበሽር እና የዑጋንዳው ፖል ካጋሜ ብቻ ሲገኙ የተቀሩት እነ ጃኮብ ዙማም ሆኑ ሌሎች ሳይገኙ ቀርተዋል።ከቅርብ ግዜ ወዲህ እንደ ቻይና ሁሉ ከህንድ ጋርም ጥብቅ ትስስር ፈጠርኩኝ እያለ የሚወተውትላት ህንድም በዝግጅቱ ላይ መሪዋ ሳይገኝ ከመቅረቱም በተጨማሪ በሀገር ውስጥ ዲፕሎማትዋን ከመወከል በስተቀር አንዳችም ባለስልጣንዋን ሳትልክ በመቅረትዋ መለስ ዜናዊ ሲመካባት እና ሲመጻደቅባት የነበረችው ህንድም ጉድ እንዳደረገችው ታውቆዋል።

አውስትራሊያ ፣ቤልጅየም ፣ጀርመን ፣ካናዳ፣ህንድ፣ጣሊያን ፣ማሌዥያ፣ሜክሲኮ ፣ብራዚል፣ስፔን ፣ስዊዘርላንድ፣ናይጄሪያ፣ደቡብ አፍሪካ ፣ታንዛኒያ እና ሌሎችም ሀገራት መሪዎች በጉባዔው ላይ ይገኛሉ ተብሎ ተጠብቆ የነበረ ቢሆንም አንዳቸውም ሳይመጡ ቀርተዋል። መለስም ዝግጅቱን ካስጀመረ በሁዋላ ጥሎ ወደ ቤተ መንግስት እንደተመለሰም ለማወቅ ተችሎዋል።

ህዝቡ ወያኔ በሚፈጥራቸው ችግሮች ምክንያት በየጊዜው በሚደረጉ ጫናዎች ኑሮን መቋቋቁዋም አቅቶት እያለ እነ መለስ ዜናዊ ግን በሀገር እና በህዝብ ሀብት ያውም በመቶ ሚሊዮኖች ብር መድበው እየተጫወቱበት መሆኑ የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ነው ሲሉም የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በብስጭት ሲገልጹ ተደምጠዋል።

ወያኔ ዘረጋሁት ባለው በጎሳ ላይ የተመሰረተ ፌዴራሊዝም ስርዓት ህዝቡ ከችግር ወደ ችግር ከድህነት ወደ ከፋ ማጣት እየተለወጠ በአንጻሩ ደግሞ በረሀ አመጣሽ የወያኔ ድልብ መሐይሞች ቀፈታቸው ተንቀርፍፎ ኪሳቸው አብጦ ያለበት ግዜ ከመሆኑም በላይ ለሀገሪትዋ የጎሳ ፖለቲካ ፍጹም የማይሆን......የነበሩዋት እሴቶችን የሚያጠፋ ......የህዝቡን አብሮ መኖር የሚፈታተን... በህሉን እና ታሪኩን የሚበታትን ወያኔ ለአገዛዙ እድሜ ለማራዘሚያ ብቻ የሚሆን ነው በማለት የሀገሪትዋ ምሁራኖች አስቀድመው አስገንዝበው እንደነበር አይዘነጋም::

ክልሎች የራሳቸውን በጀት በራሳቸው ማዘዝ የማይችሉበት..... የራሳቸውን መሪ መርጠው መሾም የማይችሉበት በመለስ እና መሰሎቹ የሚሻሩና የሚሾሙበት ፌዴራሊዝም ተብዬ የወያኔ ማድመቂያ መሆኑ ገሀድ የወጣ መሆኑ አይካድም::